

# የሚሲዮናዊ የህይወት ታሪክ

**ግላዲስ አይልዋርድ**
**ልደት: 24-02-1902**
**ሞት: 03-01-1970**
**የትውልድ ቦታ: ኤድመንተን, እንግሊዝ**
**የሚሽን ቦታ: ቻይና**

**የእግዚአብሔር ጥሪ በቀላሉ የሚጣል ደስታ አይደለም።**

ያለ ምንም የገንዘብ እርዳታ ወደ ሩቅ ቦታዎች ብቻህን መሄድ እና በማታውቀው ቋንቋ በማታውቃቸው ሰዎች መካከል ማገልገል ትችላለህ? ከሀገር ሀገር ብቻዋን በአደገኛ መንገድ እያቋረጠች፣ የመጨረሻ መድረሻዋ ወደ ሆነችው ቻይና ለመድረስ ተስፋ ያላጣችው፣ ግላዲስ ሜይ አይልዋርድ ለጥሪዋ የማይተመን ዋጋ ከፍላለች።

ከሰራተኛ ቤተሰብ የተወለደችው አይልዋርድ በ14 ዓመቷ ትምህርቷን አቋርጣ የቤት ሰራተኛ ሆና ስራ ጀመረች። በአንድ ወቅት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቻይናዊያን ወንጌልን ሰምተው እንደማያውቁ አነበበች። ወዲያው ወደ ቻይና የሚጓዙ ሚሽነሪዎችን ተቀላቀለች፣ ነገር ግን የቻይንኛ ቋንቋ በመማር ብቃት ማነስ የተነሳ ከሶስት ወር በኋላ ውድቅ ተደረገች። ነገር ግን እነዚህ አለመሳካቶች በውስጧ ያለውን የሚቃጠል መሻት ማስቆም አልቻሉም።

ወደ ቻይና ለመሄድ የሚያስችላትን ገንዘብ ለመቆጠብ የቤት ሰራተኛ ሆና መሥራቷን ቀጠለች። እ.ኤ.አ.1930 በመነሳት ርካሽ የሆነውን መንገድ በመምረጥ ረጅሙን የቻይና ጉዞ ጀመረች፤ ብዙ አደጋዎች እና መሰናክሎች ቢገጥሟትም በመጨረሻ ያንግቼን ከተማ ደረሰች። ከእዚያም ከጄኒ ላውሰን ጋር በመሆን፣ የአካባቢው ነዋሪዎች ጥላቻ ቢኖራቸውም ቻይናውያን ተጓዦችን በ"Inn of Eight Happinesses" በኩል ማግኘት ችላለች። የእስረኞች እና ወላጅ አልባ ህጻናት ህይወት እንዲሻሻል ሰርታለች፤ ከመንግስት ጋር በመሆን፣ የቻይናውያን ሴቶችን 'እግር የማሰር' ልማድ እንዲያቆም መርዳት ብቻ ሳይሆን የወንጌልንም ዘር ዘርታባቸዋለች።

በ1937 የሲኖ-ጃፓን ጦርነት ሲጀመር "ክርስቲያኖች ፈጽሞ አያፈገፍጉም" ብላ በማመን በቻይና ቆይታዋን ቀጠለች፤ በጦርነቱ ወቅት፣ በአደጋዎች መካከል ወደ 100 የሚጠጉ ወላጅ አልባ ሕፃናትን ወደ ሲያን ይዛ ሄደች በደረሱም ግዜ ከድካም ብዛት ወደቀች። በ1948 ኮሚኒስቶች በቻይና ላይ ሲገዙ ሚስዮናውያንን በጥብቅ ይከታተሉ ነበር። ምንም እንኳን ፈቃደኛ ባትሆንም፣ በጓደኞቿ አስገዳጅነት አይልዋርድ ቻይናን ለቃ ወደ ትውልድ አገሯ ከ17 ዓመታት በኋላ ተመለሰች። ነገር ግን ከልቧ ጩኸት የተነሳ ወደቻይና ለመመለስ ብትፈልግም የቻይና ኮሚኒስት መንግስት ግን ፍቃድ ከልክሏታል። ስለዚህ፣ ወደ ሆንግ ኮንግ ሄዳ በመጨረሻ በ1958 በታይዋን መኖር ጀመረች። እዚያም ግላዲስ አይልዋርድ የተባለ ወላጅ አልባ ህፃናትን ማሳደጊያ አቋቁማ እስከ መጨረሻ እስትንፋሷ ድረስ ወላጅ አልባ ለሆኑት ሰራች። ወዳጅ ሆይ፣ እግዚአብሔር በሚመራህ መንገድ በመቀጠል መከራዎችን ለመታገሥ ፈቃደኛ ነህ?

ጌታ ሆይ ጥሪዬን እንዳውቅ እና እስከ መጨረሻ እስትንደፋሴ እንድኖረው እርዳኝ። አሜን!

እጣሪ:- ዶክተር ሄፕሲባህ ሴልቫም